# ሐመልማሉ አዳም
## ተሻለ ከበደ

ቀጠሮ አለን፤ ከሥነ- ጹሑፍ ጠቢቡ አዳም ረታ ጋር ፤ ቀኑ ማክሰኞ ኅዳር 24 /2017 ዓ.ም ነው። ከባቢው ብርሐን ለብሷል። አዳም ጥቁር ሹራብና ከስክስ ጫማ አድርጓል። የሆሊውድ አክተር የምታስመስለውን ጥቁር መነጽሩን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጧታል። እንደደረስን ከመልካም ፊቱ ላይ ፈገግታ ደርቦ ተነስቶ በእቅፍ ተቀበለን። ባየሁት ቁጥር በመጽሐፉ " አውራጃ የሚሸፍን ትከሻ..." ያለውን ያስታውሰኛል። አዳም ባለሰፊ ትከሻ ነው፤ ሲያቅፍም ሞላ አድርጎ ነው።

" ምን ትፈልጋለህ?" ለሚለው ግብዣችን፤ የአዳም መልስ "ባቅላቫ " የሚል ነበር። ታዲያ ለምን መስቀል ፍላወር ወደሚገኘው ኮንዲቶራይ አንሄድም በሚለው ተስማምተን ታየም ኮፌን ትተን ወጣን ፤ መስቀል ፍላወር አካባቢ ኮንዲቶራይ የተባለ ኬክ ቤት ውስጥ ተሰየምን። እኛ ሶስት ጎረምሶች ኬክ ፣ አዳም ደግሞ ባቅላቫ እየበላን ጨዋታው ተጀመረ።በቀኙ በኩል ተቀምጬ በዓይኑ በኩል ያየኋት ነፍሱ እንደ ጥር ስማይ ንፁህ ነበረች። ታዋቂው ፈረንሳያዊ ደራሲ ቪክቶር ሁጎ ስለ ሌላኛው የሀገሩ ልጅ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ተደናቂ ደራሲ ሆኖሬ ዲ ባልዛክን ለመግለፅ የተቀመጠበትን ነገረ ሃሳብ ወደ እዚህ ልሳብና ላምጣው፡-

"He is the historian of the heart, the anatomist of society, the poet of ambition and despair."

አዳም ለእኛ ከባልዛክም በላይ ነው። የልባችን ቁስል ወይም የነፍሳችን ስቃይ ተራኪ ብቻ አይደለም፣ ከዛችው ስቃያችንና ቁስላችን ህይወትን እንደ አዲስ ይፈጥራል። የተስፋችን ሞት ከብስባሹ አውጥቶ በረቂቅ ስነ-ጥበባዊ ብርሃን ጭለማውን ገፎ ወደ ሕይወት የሚያሻግራት ልዕለ-ሰብ ነው። በአዳም ድርሰት ውስጥ ሕይወት የሌለው ነገር ምን አለ? መንገዱ ፣ አቧራው ፣ የመንገዱ ሙብራት ፣ ድንጋዩ ፣ እንጨቱ ፣ ህንፃው ፣ ቤቱ ፣ ምግቡ ... ሁሉም ሕይወት አለው። አዳም የሕይወት ደራሲ ነው። ለዚህም ነው ሕይወት ላይ የገነነ ውና የተሾመው። የአዳም ስራዎች ግባቸውን በቀለም ይወከሉ ከተባለ ሐመልማል አረንጓዴ ነው ፤ የሕይወት ቀለም ነውና።

አዳም የዘመናችን ተጋዳሊ ነው። የስነ-ጽሑፍ ማዕምሩ ቴዎድሮስ ገብሬ ስለ ሐዲስ ሚቶሎጂ (ዘመናዊ ተጋዳሊ) ሲያትት " ... የሐዲስ ሚቶሎጂ ዓቢይ ጉዳይ የግለሰቡ ልቡና እና ዩኒቨርሳዊ ቁርኝት ነውና ለነባሮቹ (ለብሉይ ሚቶሎጂ) 'ፍፁማን' እውቅና አይሰጥም። እንደ ብሔርተኝነት ፣ ጎሰኝነት ፣ መልክአ ምድራዊ ውሱንነት ያሉ ጽንስ ሐሳቦች በሁለንታዊ ፣ ዓለም

አቀፋዊ ባሕሎች መረታት አለባቸው ብሎ ያምናል" ይላል (በይነ ዲሲፐሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ ፥ 94- 95) ።

በዚህም ምክንያት አዳም " የሃሳብ ማዕከል " እንዲሆን እፈልጋለሁ። ለምን? ቢያንስ ቢያንስ በሶስት ማዕከላዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ምክንያት፡-

አንደኛ የወል እሳቤያችን ነፍስያ ከአዳም የብዕር ምጥ ስለምትከፈል ፤ ሁለተኛ ህዝባዊ ፖለቲካችን በአዳም የስነ- ጽሑፍ ፍልስፍና ሐርነቱን (Emanicipation) ስለሚጎናፀፍ ፤ ሶስተኛ ማህበረሰባዊ ውጥንቅጣችን በትስስር ፍኖት በአዳም ሰራሽ ሕጽናዊነት ህልውናውንና ድኅነቱን ስለሚያገኝ ነው።

ይህን የተመረጠ ውይይት እናንተ ጋር ለማድረስ የመረጥኩት ዘዴ እንደ ወረደ ባደረግነው የውይይት ቅርጽ ነው። ለየት ቢልባችሁ ሕግ የተከተለ ቃለ መጠይቅ ሳይሆን ለመጨዋወት በተገናኙ አራት ሰዎች መሐል የተደረገ ውይይት መሰል ጨዋታ በመሆኑ ነው። ውይይታችንን የግል ምልከታ አድርጌ ላለመፃፍ የወሰንኩበት ምክንያት ደራሲውን በእኔ አተያይ እንዳይቀነበብና አንባቢዎችም የደራሲው ምላሽ በየራሳቸው መንገድ እንዲረዱትና ለአተረጓጎምም ክፍት ለማድረግ በማሰብ ነው። በተረፈ ግን ቀስ ተብሎ እየተብላላ፤ ከተቻለም ምን ማለቱ ነው? ተብሎ እየተጠና ቢነበብ እጅግ ፍሬያማ ነገር ይወጣዋል ብዬ አምናለሁ።

በውይይቱ ላይ የተሳተፍነው—እኔ ፣ ጋዜጠኛ ሐብቱ ግርማና የቴአትር ባለሙያ የሆነው ገዛኸኝ ድሪባ ነበርን።

አዳም ጨዋታችን ለአንባቢ እንዲደርስ መልካም ፍቃድህ በመሆኑ በቅድሚያ በአንባቢዎቻችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

ሀብቱ:- አዳምሻ አራታችንን የሚያስማማ ተረት እንዴት መስራት እንችላለን? እሱን ለመስራት ነው መታገል ያለብን ብዬ ነው ማስበው። "ፍትሃ ነገስቱን" የሚቀበል አለ ፤ "ብሔር ብሔረሰቦችን " የሚቀበል አለ ፤ "መሃል ሰፋሪም " አለ። ስለዚህ አዲስ ታሪክ መፍጠር ያስፈልገናል በተጨማሪም ለህልውናችን አዲስ መዋቅር መፍጠርም ግድ ይለናል (so we need to make a new story and new structure for our existence) ። ምን ይሰማሃል በዚህ ጉዳይ?

አዳም :- አቅጂ አልነሳም ፣ ይሄን ልስራ ያንን በማለት አይመጣም ! ልብ ወለድ ስፅፍ ይሄን ተረክ (story) ልፃፍ ብዬ አልቀመጥም። የሆነ ተረክ አለ እሱን ትተርካለህ። አቅደህ

አትፅፍም ፤ ዝም ብዬ ሰኖር ተረክ ያጋጥመኛል እፅፋለሁ። እንጂ እንዲህ ማድረግ አለብኝ ብዬ አልዘረዝርም ። ያ' ሌላ መንገድ ነው ፤ የእኔ አይደለም። እኔ በስፖንታኒየስ (Spontaneous) በኩል ነኝ። የሆነ የተያያዙ ተረኮች ይገጥሙኛል እነሱን እሰራለሁ። ጠዋት ተነስቼ ድርሰት ልፃፍ አልልም ፤ተነስቼ ወንበሬ ላይ አልቀመጥም ፤ ልፅፍም እችላለሁ ፣ ቶሎ ልነሳም እችላለሁ፣ ወይም ላዛግ እችላለሁ አላውቅም ሃሃሃ ....
የስነ ጥበብ ተረካ (Art narrative) እና የፖለቲካ ተረካ (political narrative) የተለያዩ ናቸው። የጋራ ነገር ሊኖራቸው ይችላል።

ተሻለ፡- በዚህ ዘመን ስነ ጥበብ ራሱ ፖለቲካ አይደለም?

አዳም፡- ሁሉም ነገር ፖለቲካ ነው። ንድፈ ሀሳብ (theory) እና ፍካሬ ግን የየራሳቸው ባህሪ አላቸው። ግን እንዴት ነው የተወከሉት የሚለው ጉዳይ ነው ወሳኙ ፤ እንጂ ሁሉም ቦታ ፖለቲካ አለ። ምድር ላይ ስትኖር ተረካ (Narrative) ውስጥ ሁሉም ነገር አለ። አየር ፣ ሳይንስ ፣ ሃይማኖት ብቻ ሁሉም ነገር አለ።
.... እዛ ውስጥ በማርያም ሚምል አለ፤ ከሶስት ሺህ ዓመት በፊት ግን አልነበረም ወዘተ ...

ሀብቱ፡- አሁን እንኳን በራሱ ሚምል ነው ያለው ሃሃሃ ..

አዳም፡- ጥያቄህን ግን መልሼልሃለሁ?

ሀብቱ፡- መልስህን ሳይሆን መንፈስህን ነው የፈለግኩት፤ ደርሶኛል ቆንጆ ነው...
ልክ አሁን እንዳለንበት የሚያደክም ዘመን .... ማለትም የዛሬ 40 ዓመት የተከሰተ ነገር እንደገና ሲከሰት ይደክማል ሰልችት ይላል። አንዳንድ ቀን መውጪያ ቀዳዳ ይጠፋል። እንደው መውጫ የሚሆን አንተ ያየኸው መንገድ ይኖር ይሆን ፤ የ ታዘብከው? ....ጥሩ የምታሰብበት የሚመስለኝ የአብዮቱን መንገድ የምታውቀው ነው። እኛ ከአብዮቱም የባሰ የቀውስ መንገድ ላይ ስላለን በወል እንደዚህ አይነት ዘመንን እንዴት ነው መሸከም ያለብን? እንዴት ነው ኀበዝ መሆን ያለብን? እንደ ግለሰብም እንደ ማህበረሰብም?

አዳም፡- እኔ የማደርገው ዝም ብዬ ማየት ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ክስተቶችም ሆኑ ሁነቶች ጥልቅ ሀሳብን ይጠይቃሉ ፤ ማሰብ አለብህ ፣ መመርመር አለብህ። ሁሉም መድኃኒት ፈላጊ መድኃኒት ቀማሚ አይለም። እኔ በቃ ተረክ እፅፍልሃለሁ ፤ በዛ ተረክ ውስጥ የሆነ ነገር ለመንገር እሞክራለሁ። በተረኮቼ ውስጥ አልወግንም። በዛ ውስጥ የማስታውሰውን ነው የምፅፈው። ምናልባት እኔን ራሴንም የሚያስከፋኝ ሊሆን ይችላል። ግን እዛ ውስጥ ፍርድ ሳልወስድ ማስቀመጥና ትንቢታዊ (predictive) እንዲሆኑ የማድረግ ነው የእኔ ስራ። የእኔ

ድርጊት የመተረክ ፣ አስተማስሎ (Representation) የመስራት እና መጪውን የማሳየት ነው። ከዚህ በተረፈ ነብይ (የብሉይ ዘመን ነብይ) ነው የሚመልሰው ... ባቅላቫ መብላትም ሕይወት ነው ሃሃሃ ...

ሀብቱ :- ጉዞውን እንወደዋለን። ትግሉ ፣ መማሩ ፣ መውደቁ፣ ተጋድሎ ቆንጆ ነው። ተጋድሎ ነው አይደል ሰውን ሰው ያደረገው? ተመስገን ማለቱ ፣ ሌሊት እንቅልፍ ማጣቱ ፣ ጧ! ብሎ መተኛቱ አይደል?

አዳም:- እርግጠኛ አይደለሁም .... የግድ መስቃየት አለብህ?
ይሄ ድርጊት አዲስ ፍልስፍና የመፍጠርም ሊሆን ይችላል። ከችግሩ ለመውጣት የሚያፈናጥርህ እሳቤ ወይም የአስተሳሰብ መንገድ (Concept system) ፈጥረህ አዲስ አለም የማበጀትም ሊሆን ይችላል።
ይሄን ሁሉ ግን አንድ ደራሲ ላይመልሰው ይችላል። ከእኔ መጠየቅ ያለብህ ሀቀኛ (authentic) መሆኔን ነው። የምትፈጥራቸው ገጸ ባህርያት ሀቀኛ መሆን አለባቸው... ከአንድ ደራሲ ሁሉንም ነገር መጠበቅ ሊያስቸግር ይችላል።

ገዛኸኝ:- ድርሰቶችህን ሀቀኛ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? ድርስቶችህን ስናነብ ህይወት አላቸው። ማለት ቴክስት ብቻ አይደሉም፤ በተለይ የገጸ ባህርያት ግንኙነትን ብንመለከት ጥርት ያለ የህይወት መሰናስል አለው ፤ ሕይወትን ነው የምትፅፈው። በዚህ ልክ እንዴት ሊሳካ ቻለ?

አዳም:- በስሜት ሕዋሳቶቼ ነው የምረዳቸው ፤ በቃ ያ' ነው ለእኔ መለኪያው። ርቀት ከተሰማህ ግን ውስጥህ አልደረሰም፤ በስሜትህ አትለካውም። ግጥም ሳነብ በሃሳቡ ሳይሆን በስሜት ሕዋሳቶቼ ነው የምለካው (I just Feel it) ፤ በቃ ውስጤን ሊነካኝ ይገባል። ውስጥህ ሲነካ ፀጉርህ ይቆማል ፣ የሆነ አይነት መመስጥን ይፈጥርልሃል። የሆነ ጥልቀት ያለው ህመምም ይሁን ደስታ ይጋባብሃል ፣ እንደዛ ከሆነ ልክ ነው። በአመክንዮ ላላስረዳህ እችላለሁ ። ሃያሲ ሌላ ነገር ነው ፤ የሚያይበት መንገድ ይለያል። መዓት መፅሐፍ አለ የሚነበብ ግን አይነካህም ፤ ሁሉም አይዳብሱህም።

ገዛኸኝ:- ይሄንን የተረዳሁት እንዴት ነው? ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድን በዘመኔ ቢያንስ ሶስቴ አንብቤዋለሁ። በሶስቱም ጊዜያት የተለያየ ነገር ነው የተረዳሁት፤ ይሄ ደግሞ ህይወት ካልሆነ እንደ እድሜ የሚነሳ ወይም የምንገነዘበው ነገር አይኖረውም።

አዳም:- ሀቀኛ (Authentic) ማለቴ .... እውነታን ወክለሃል ብሎ የሚነግርህ ካለ ያ' ህይወት ነው። ለምሳሌ እዚህ ውስጥ የሰባት መንገዶች ወግ (ጠረጴዛው ላይ ይወስዳል መንገድ

ያመጣል መንገድ መፅሐፍ ነበር) እውነታውን አይተኻል? አላየህም ! 1967 ዓ.ም ነበርክ? አልነበርክም ! ግን የሆነ ነገር ከመፅሃፍ ያገኘህ ይመስልሃል ወይም አግኝተኻል። ትርጉም (meaning) እርስ በራሱ የተያያዘ ነገር አለው ፤በስሜት ትደርስበታለህ። ለዚህ ነው የስሜት ሕዋስህን መረዳት አስፈላጊ የሚሆነበት ምክንያት ... ይሄ ሃያሲ የሚስጥህ ትርጉም አይደለም። ሃያሲ ከሰጠህም የሚሰጥህ አለማቀፋዊ ትርጉም ነው። ንባብ ላይ የሚያጋጥምህ ነርቭህ ውስጥ የሚቀመጥ ስሜት ወይም ተመስጦ (affection) ነው።

ተሻለ፡- ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ በጣም ከባድ ድርሰት ነው። በተለይ የሰባት መንገዶች ወግ በጣም ከባድ ስራ ነው። እኔ ሳነበው እውነት ለመናገር ልናገረው የማልችለው ዓይነት ህመም ነበረው፤ የተወሰነ ቀን ተደብሬያለሁ ፣ አዝኛለሁ። ስሜቴን ክፉኛ በጥብጦት ነበር። አሁንም ሳነበው ያው ህመም ተመልሶ ይቀስቀሳል።

እኔ የአብዮቱን ዘመን በግለ ታሪክ ፣ በአካዳሚክ ስራዎች ፣ በፍልስፍና ስራዎች ፣ በስዕል ኤግዚቢሽኖች ፣ በአብዮቱ ዘመን በነበሩ ጋዜጦችና የፓርቲ ልሳኖች ሳይቀር ለማንበብ ያቅሜን ሞክሬያለሁ። ያንተን ድርሰቶችን ያህል የሚያነቃንቀኝ ግን አላገኘሁም። የአንተ ስራዎች ናቸው መለኪያ የማደርጋቸው። ለዚህም ደራሲው ያንን ሁነት ወይም ክስተት ሲፅፍ ተራ የመፃፍ ድርጊት ብቻ አይደለም። ህይወት ሆነው የተገለጡበትን መንገድ እና አቅም ጭምር ነው እኔ የተገነዘብኩት። ምክንያቱም አንድ ተረክ (Story) አለ ተረካ (Narrative) የማይቆም ከሆነ እዛ ተረካ (Narrative) ውስጥ ርዕዮተ ዓለም (Ideology) ፣ መዋቅራዊ ስነ ዕውቀት (structural epistemology) ፣ ባህላዊ ልምምዶች እና ጉዳዮች ( Cultural Practices and materials) ሳይወዱ በግድ ይገባሉ። በተጨማሪም የደራሲው መሻት (intention of the author) ይኖራል። እኔ ደራሲው ሞቷል (The Death of the Author) በሚባለው ሀሳብ አልስማማም። ይህ ከሆነ ደግሞ መጪውን የማለም ብሎም ነገን የመስራት ምኞቱ አብሮ ይቀሰቀሳል ወይም ይጠ'ራል (Imagined future) ።

አዳም፡- መኖር አለበት ፤ እንዳለ ሁነቱን ብቻ ካስቀመጠ የአስተማስሎ (Representation) ስራ ብቻ ይሆናል። ከዛ በመውጣት እመርታ (Emergent) የሆነ ነገር ያስፈልጋል። ምናባዊ ነገር ስታስገባ የዛ ተረክ የመባያ ጉዳዮች (motives value) ይጨምራል፤ ውጥረቱ (Intensity) ይጨምራል። ምክንያቱም መነሻው ሀቀኝነት (authenticity) ስለሆነ ነው፤ እናም ትቀበለዋለህ። እመርታ (Emergent) ገጸ ባህርይ ሲሆን ትምቢት ይኖረዋል ግን መነሻው ሀቀኝነት (Authenticity) መሆን አለበት።

ለአንዳንድ ሰዎች እርካታ የማይስጥበት ምክንያት ምንድን ነው? .... የሆነ የሚያሸንፍ ነገር ይፈልጋሉ። ውስጣቸው መከፋፈል ይኖርና "የእኔና የእሱ " የሆነ አይነት ክፍፍል ይፈጥራሉ .... በዛም ስሜታቸውን ይጎዱታል (They Betray their feelings) ።

ማንኛውም የሰነ ጽሁፍ ወይም የስነ ጥበብ ስራ የሆነ ዐይነት የዋህነት ይጠይቃል። መነሻ ቅንነትን ይጠይቃል ፤ እንደዛ ካልተነሳ ይሞታል። እንደዛ ደግሞ ለመሆን ራስህን መተው አለብህ ፤ ራስህን እንደ ገዳማዊ መርሳት አለብህ ፤ ከራስ መፅዳት ግድ ነው። ትዕቢትህን (Ego) ቢያንስ ስትፅፍ መተው አለብህ። አለበለዚያ ነገሩን አታገኘውም (you never get the point) .... አሪፍ ብትፅፍም አይመጣም። ሌላው ራስ ወዳድ ሊሆን ይችላል ...ተጨማሪ ባቅላቫ እፈልጋለሁ ሊል ይችላል ሃሃሃ ....

ሀብቱ፡- ለምንድን ነው ትልቅ ትህትና የሚያስፈልገው? ራስን መካድ ለምን ያስፈልጋል? በተቃራኒው ተገልብጦ ኃይለኛ ፣ ጉልበተኛ ፣ እኔ ያልኩት ነው የሚሆነው ቢል ለምን ከደራሲነቱ ጋር አይገጥምለትም?

አዳም፡- እንደማስበው ከምንኖርበት ዓለም ጋር የተገናኘ ነው (I think it is connected to the universe) ፤ በሃሳብ ደረጃ ከተለመደው ተሞክሮ (Experience) መነጠል አለብህ።

ተሻለ፡- ይሄን የእሳቤ ለውጥ (paradigm shift) እንዴት አገኘኸው? ሁሉም ሐበሻ ትዕቢቱን አፍንጫው ስር፣ ንግስናውን በልቡ ይዞ የሚኖር ነው ፤ የዕድል ቀኑን ጠባቂ ነው። እኔም ብሆን ሌላው እድሉን ብናገኝ ገራፊዎች ነን። ታዲያ አንተ እንዴት በተለየ መንገድ ሄድክ? ከሃገር መውጣትህ ነው? ወይስ ሌላ ተሞክሮ አለህ?

አዳም፡- ዓለም ሰፊ ነው። ሕጽናዊነት ከዚህ ጋር የሚገናኝም ነው። ብዙ ነገር አናውቅም ፣ ብዙ ነገር አላውቅም። ላስቅህና ምን ያህል አላዋቂ እንደሆንኩኝ እንኳን አላውቅም (Even I don’t know how much I’m ignorant) ሃሃሃ ....

ስለዚህ እንዴት ነው የምታውቀው? የነገሮችን መያያዝ ትረዳለህ ... ሁለት ነገሮች ተወደደም ተጠላም በግንኙነት ህግ ውስጥ ነው የሚኖሩት (this thing and that thing they have a certain connection) እንደዛ ነው ህልውናቸው ሚያስቀጥሉት .... ደንቆሮዎች ናቸው ግን በግንኙነት እምቃት (Potential) ነው ህልውናቸው ሚቀጥለው ... ይሄን በአግባቡ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ ይሄንን መፅሐፍ ስንት ቀን ይዘኸው ዞርክ? ብልህ አታውቅም … ስንት ገፅ እንዳለው ብጠይቅህ ላታውቅ ትችላለህ … ይሄንን አንብበኸዋል? (ብለርቡን ማለቱ ነው)…ስንት ቃላት አሉት? ብልህ አታውቅም … ህይወትም እንደዛ ነው …. እናም ይሄንን መረዳት ያስፈልጋል። መፃፍ ስጀምር ነገሮችን አላውቅም ከሚል ነው የምነሳው … ስለዚህ የመፃፍ ድርጊት ራሱ የመማር ድርጊት ነው። መረዳት እና አንዳንዴም የአንባቢዎችን ነገር መከተል ….እናም በአራዳ ቋንቋ አለማካበድ ነው ሃሃ …

ገዛኸኝ፡- ብዙ ጊዜ በድርሰትህ ውስጥ ከእውነታው ዓለም ጋር የሚገጥሙ ታሪኮችን እናገኛለን። የአስተማስሎና የልዋጭ (Metaphor) ሀሳቦች እንዴት ነው ከታሪክ ድርሳናት እና ከሀቀኝነት (authenticity) ጋር የሚዋሃዱት (sync) የሚሆኑት?

አዳም፡- በእውቀት ውስጥ ሁለት ዓይነት ክፍፍል አለ ፤ ስነ ጥበብና ሳይንስ … እነዚህ ሁለቱ የተያያዙ ናቸው ለማለት ነው። በግርጌ ማስታወሻ ሃያሲ ጠቅላላ ይቀርባል … ሃያሲው ሳይንሳዊ ነገሮችን ይበረብራል ፣ መረጃ ይሰበስባል ፣ ይተነትናል ወዘተ። ዋናው ክፍል ደግሞ ሕይወት ነው፤ ስለዚህ ሁለቱንም በአንድ ላይ የማቅረብ እንዲሁም የማገናኘትም ነው ፤ የስነ ጥበብ እና የሳይንስና መጎዳኘት ነው (The integration of art and science) ።

ገዛኸኝ፡- ታክሲ ውስጥ ስንገባ ሹፌሩ መንጃ ፈቃድ ይኑረው አይኑረው አናውቅም። ይናደድ አይናደድ አናውቅም በቃ ዝም ብለን እንገባለን …

አዳም፡- መፃፍም ልክ እንደዛ ነው። በሂደት ነው የሚዳብረው፤ የተሳሳተውን ከዛ በኋላ ታቀናለህ ፣ ታርማለህ።

ተሻለ፡- የአንተ ስራዎች ግን ይሁነኝ ተብለው የሚሰሩ ናቸው። እንደውም አብዛኛዎቹ ስራዎችህ ፕሮጀክቶችም ናቸው ብል እውነት ነው ፤ ደግሞም ልክም ነኝ። በፅንስ ሀሳብ ደረጃ ብዙ ማለት ቢቻልም ….እንጀራ (ሞዴል ብቻ አይደለም) ፣ ሕጽናዊነት (ፍልስፍና ብቻ አይደለም) ፣ ታሪክም ሆነ አብዮት (የአንድ ወቅት ክስተት ወይም ሁነት አድርጐ የመተረክ ጉዳይ ብቻ አይደለም) ፣ ማህበረሰብ (የአስተማስሎ ጉዳይ ብቻ አይደለም) ፣ ፖለቲካ (ትችት ብቻ አይደለም) ወዘተ … በመሆኑም ደራሲው በደንብ አቅዶ እንደሚሰራ ግልፅ ነው ….

አዳም ፡- ሕጽናዊነት ግራጫ ቃጭሎች ላይ ያለው መግቢያ ንድፈ ሃሳባዊ (theoretical) ይመስላል ግን የጠራ አይደለም (Vague) ነው …

ተሻለ:- ይቅርታ አቋረጥኩህ ... እኔ መግቢያውን ብቻ አይደለም ያየሁት ፣ በተለያዩ ስራዎችህ ውስጥ በድግግሞሽ የተሰራበት እሳቤ ነው። አሁን ሕጽናዊነት በደንብ ተገንብቷል ፣ በሚገባ አድጓል ማለት ይቻላል። ለዚህ ማሳያ እቴሜቴ ሎሚ ሽታ ነው። በሕጽናዊነት ግንባታው እጅግ የተዋጣለት ብሉይ ስራ ነው።

የአንተን ሕጽናዊነት ከፍሬንቾቹ ድህረ መዋቅራዊያን (Post Structuralist) ከሆኑት ጁሊያ ክሪስቴቫ ፣ ሮላንድ ባርቴዝ ፣ ዣክ ዴሪዳ እንዲሁም በመዋቅራዊ (Structuralist) እሳቤ ውስጥ ሕጽናዊነትን ካበለፀገው ዤራርድ ዤኔት በእጅጉ የተለየ ነው። ከፈረንሳይ ስንወጣ ደግሞ ሩሲያዊው ፈላስፋና የስነ ጽሑፍ ሊቁ ሚኻኤል ሚኻይሎቪች ባክኽቲን (Mikhail Mikhailovich Bakhtin) እሳቤ የተለየ ነው። እስካሁን ባለኝ ንባብ አንተ በገነባኸውና በስራህበት መልኩ የተጠቀመበት ማንም የለም። በመሆኑም የአንተ ፍልስፍና አዎንታዊነትና ውጤታማነትን በማካተቱ ፍልስፍናዊ እሳቤው በእጅጉ ጠቃሚ ነው (Your "Hitsinawinet" is incredibly Positive and Productive) ። በመሆኑም በአንድ በኩል ለማህበረሰባችን ፍኖትን የሚሰጥ ሲሆን በሌላ በኩል ካየነው ደግሞ ለፖለቲካችን ሐርነት አዋላጅ (The cradle of public politics) አድርጌ ነው የማስበው። ልፋትህ እጅን በአፍ የሚያስጭን ነው ፤ ሲበዛ ይደንቀኛል። በዚህ ልክ ይቻላል እንዴ?

አዳም:- መሰረት ያስፈልግሃል አይደል? የሆነ የምትቆምበት ነገር ያስፈልጋል፤ አለበለዚያ ነገሩ ሁሉ ይበታተናል። ግን ዝም ብሎ ይሄ ነው መነሻዬ ለማለት ሳይሆን በአግባቡ የተጠና እና በዕውቀት የለውጥ ሂደት (knowledge Dynamics) ውስጥ የሚገለጥ መሆን አለበት። እንጂ ተራ የመቅዳት ጉዳይ ከሆነ ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል ፤ ደመ ነፍሳዊ ሃሳብ (Zombie Concept) የማራባት ጉዳይ ይሆናል።

ተሻለ:- ከዚህ ወደ አውሮፓ ስትሄድ የነበረውን ማህበረሰብ ሆላንድ እያለህ ከነበረው ፣ አሁን ደግሞ ካናዳ ካለው ማህበረሰብ አንፃር የእኛን ማህበረሰብ እንዴት ታየዋለህ? አሁን እኛ የቆምንበት በንፅፅር ምን ይመስላል? አማራጭ ማህበረሰብ (Alternative society) የመፍጠር እቅድ አለህ?

አዳም :- ስራዎቼ አማራጭ ሚቶሎጂን ይፈጥራሉ ... ሁሉም ተረክ ሚት እኮ ነው (Every story is a myth) ። የስፋትና የጥልቀት ጉዳይ ነው። ግን አሁን ያለው በጣም ውስን (Localized) ነው ፤ ግለሰባዊ ነው። በሰፊው ለመጠቀም የሃገራችንም ሁኔታ ወሳኝነት ይኖረዋል። የፖለቲካ አቅማችን ፣ የኢኮኖሚ አቅማችን ፣ የዲስኮርስ አቅማችን፣ የእውቀት ነፃነታችን ነው ከዚህ አውጥቶ ለዓለም የሚያሰራጨው። አየህ እንደ አሜሪካ ምናምን አቅም

ቢኖረን ኖሮ ከ “ ኢዮር “ የመጣን ነን ልንል እንችላለን። ጉራ ለመንፋት እንኳ አቅም ይጠይቃል ሃሃሃ ...

ሀብቱ፡- አዳምሻ ጨዋታ ለምን ይማርክሃል? ስትኖርም፣ ስትጽፍም ለምን ለተረክ ስትል ተሸነፍክ? ለምን ዋነኛ መገልገያ መሳሪያህ (instrument) ሆነህ?

አዳም፡- የምትኖረው ነው። ሁሉም ነገር ተረክ ነው (Everything is a story) ። ዋናተኛ መዋኘት አለበት፤ ሯጩም መሮጥ አለበት፤ ጸሐፊው መጻፍ አለበት ሃሃሃ... ተረክ የምናብ ጉዳይ ነው ፤ ያ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነው።

ገዛኸኝ፡- አካልህ ይጠብኻል?

አዳም፡- ምናልባት ሊሆን ይችላል። ቆዳዬ በጣም መለጠጥ አለበት ፤ ወይም እፈልግ ይሆናል ሃሃሃ..

ሀብቱ፡- ሙዚቃ ወይም አልበም የምትወደው? ... መቼም " ዞራ ዞራ የእኔ ነች " የሚለውን አላደመጥክም ... መፅሃፍስ?

አዳም ፡- ብዙ ጥሩ ጥሩ ሙዚቃ አለ ፣ ጥሩ ጥሩ ወጣቶችም እየመጡ ነው። አሁን አንተ ያልከው ዘፈን ግን ያንተ መሆን አለበት ...

መፅሃፍ? ... AI ን ጠየቅኩት መጽሐፍ ከየት ከየት ላገኝ እችላለሁ ብዬ .... ዝርዝር ሰጥቶኝ pdf driveን ዘለላት .... ወሳኝዋን! ...What about Pdf drive አልኩት? ...ስለ እሱ መረጃ ልሰጥህ አልችልም አለኝ .... ለምን ጌታዬ (Why sir) ልበለው? ለምን ማሽን (Why machine) ልበለው? ሃሃሃ... አይ እዛ ከገባህ የቅጂ መብት (Copy right) ማክበር አለብህ ምናምን አለ ... ተወው AI is not Free .... ነፃ አይደለህም አልኩት...

ሀብቱ፡- ተበላህ "AI " አትለውም ነበር ሃሃሃ ...

አዳም፡- ወይኔ በአማርኛ ተበላህ ብለው አሪፍ ነበር ሃሃሃ ...እኔ ልጠይቃችሁ ለምንድን ነው የእኔን መጽሐፎች የምትወዱት? (Why do you like my books?) መልሱልኝ!

ሀብቱ፡- አሪፍ ጀለስ ነህ! ጀለስህ እንዴት ነው የሚያውቅህ? የተቀደደ ካልሲህን ያውቅልሃል ... ያቺ የሆነ ቀን የሳምካትና ላሽ ያለችህን ልጅ ያርፋታል ፣ በጣም ሲቸስትህ ከጓደኛህ ጋር የትኛው ምግብ ቤት ሄዳችሁ እንደምትፈወሱ ያውቃል። አዳም እንደዛ ነው ... በልደታና በመርካቶ መካከል ያለ አሪፍ ጀለስ ነው ሃሃሃ

አዳም፡- አሪፍ መልስ ናት ግን እዛ Facebook ላይ የፃፍከው አይነት አይደለም።

ሀብቱ፡- እኔ ከበድ ባለ መንገድ ማሰብ እወዳለሁ። ስለ ሀገርን መልሶ ስለ ማዋቀር (Restructuring of nation) ፣ ማህበረሰባዊ ከለላ (societal Protection) ፣ ከኅሩያን ማዕከላዊነት (Elite Centric) ከመሆን የወል ተዛምዶነት (Communality of Culture) እፈልጋለሁ .... በተጨማሪ ብዙኃኑ ሕዝብ (Mass Population) የሚኖርበትን ጥበብ ደግሞ እፈልጋለሁ። ከዛ ቆንጆ ምልከታ (Observation) ያለው ጠባቂ ...ጥሩ ጠባቂ (patron) እወዳለሁ ... አዳም ያ' ጥበብ አለው ብዬ አስባለሁ። ለዛ ነው አዳምን የምወደው ...

ሁለተኛ ይሄ ሃገር ... ገራኣልታ ሄጄ አውቃለሁ ፣ ወለጋ ሄጄ አውቃለሁ— በ1 .25 ሳ ቡና ጠጥቻለሁ፣ አርባምንጭ ሄጃለሁ— ናይል ፐርች የተባለ ዓሣ በልቻለሁ፤ አዲስ አበባ ርቦኝ ምናምን አውቃለሁ ... አዳም ይሄንን በብዝኃነት ተረካ (multiplicity narrative) ውስጥ በደንብ አድርጎ መስራት ይችላል። ግን አዳም ይከብደኛል። ትሁት ሆኜ አይደለም... እኔ ሳስብ በጣም ፖለቲካ ይጫነኛል። የእኛ ሀገር ፖለቲካዊ እሳቤው በእጅጉ የሚያይልበት ነው ... የተጎዳውም ለዛ ነው ... ያንን የፖለቲካ ጉዳይ ወስደን ፖለቲካዊ ያልሆነን ነገር ልንስራባት ይገባል (We need those Political element to make apolitical) ብዬ አስባለሁ። በጣም ፖለቲካዊ ጉዳዮችን እየፃፈ ተራ እና ረብ የለሽ ማድረግ ይችላል ማን? አዳም ! ያንን እንደ አንድ የአዲስ ሚት መስሪያ (New Myth making) ሃሳብ አድርጌ አስበዋለሁ። በጉዳዩ ላይ ደጋግሜ ባሰብኩበት ቁጥር ይበልጥ ስሜት ይስጠኛል።

ገዛኸኝ፡- የአብዮቱ ጉዳይ እንደ ጀብድ ነው ሚታየው በተለይ በእኛ ትውልድ አይን .... የጀግንነት እሳቤ (Heroic Concept) አለው ... መረቅ እስኪወጣ ብዙ አብዮት ተኮር ታሪኮችን አንብበናል ... የኢህአፓን ጉዳይ በቁጭትና በደጋፊነት ጎራ እስክንከፈል ሁሉ ያነበብናቸው ታሪኮች አሉ። ምክንያቱም ጣፋጭና መሳጭ ታሪኮችን ነው ሚሰጡን። መረቅ ለማንም የማይወግነውን አላዛር'ንና ዝም ብሎ የሚኖረውን ማህበረሰብ አሳይቶኛል። መረቅ ለእኔ ደፋሮች የሚፅፉት የታሪክ መፅሐፍ ነው። ደፋሮች ናቸው ያንን ክፍተት የሚሞሉት እንዴት? በሁለት በኩል ስለሚሞቱ ... እናም የተቀደሰ ሞት ነው ለእኔ ... ተባረኪ ዴሞክራሲያን ማራገቢያ ስታደርገው አስባታለሁ... ከየት ወዴት እንደመጣች አስባለሁ ...

እንሞትለታለን የምንለው ነገር የሆነ ሰዓት ላይ እንደተራ ነገር እሳት ማያያዣ ልናደርገው እንችላለን ... መረቅ ግን የህይወት መንገድ ነው ብሎ የማንሳት እውነታ አለው፤ እኔ አዳምን የምወደው ታላላቆቻችን የሚደብቁንን ፍርሃታቸውን ፣ መውደዳቸውን ፣ ከጀብዳቸው ውጪ ያለውን ሕይወታቸውን ... አዳም ይነግረናል ... ባንተ ድርሰት ውስጥ ራቆታችንን ነው ምንገኘው።

ስዕልና ቀለም ትወዳለህ? ከስዩም ወልዴ በኋላ ሂስን ያዘሉ፣ ስለ ስዕል የሚያብራሩ ፅሁፎች በድርሰቶችህ ውስጥ አሉ። የምናብ መስፋት ነው ወይስ ስዕል ነፃነት ስለሚስጥህ ነው?

አዳም፡- ገፀ ባህሪው ሊሆን ይችላል ... የተለያዩ ዘውጎችን (genres) ለማገናኘት ሊሆንም ይችላል። ስትፅፍ ምስል አለ። አዕምሯችን ውስጥ ንድፍ (sketch) አለ ... ስዕል የትም አለ. ... በግንዛቤ ወይም በመማር (cognitive processes) ሂደት ውስጥ ስዕል ይቀድማል። ፊደል ሳንቆጥር ነው ፀሐይ የምንሞቀው . ... ግን እንደማንኛውም ገጸ ባህርይ ሊገጥምህ ይችላል። ቀጥታ የማደርገው ምንድን ነው...ራሱ ልዋጭ (metaphor) ነው። እዛ ላይ ያለ አንድ የስዕል ስታይል ሕጽን ነው። ባዶ ቦታ የመሙላትም ነው። እንደ ደራሲ ነው ማለት ነው። ሌላው ጉዳይ ሂስ ነው። የስዕል ሂስ ብዙ ጊዜ አያጋጥምህም... ያኔ ያ'ታሪክ ሲከሰት እኔ አላየሁም... ባይ እንኳን ይፈቀድልኛል... ድርጊቱ ስዕልና ቋንቋን የማያያዝ ነው ፣ ስዕልና ሕጽናዊነትን ማያያዝ ነው ፣ ነገረ ዓለሙ በሙሉ የተያያዘ ነው። አንዱ የአንዱ ነፀብራቅ (reflection) ይሆናል።

ተሻለ፡- ስለዚህ መፅሃፎችህ የተገነቡት በሕፅናዊነት መሰረት ላይ ነው ማለት ነው? ለምሳሌ ሺ አምባዎች የተገነባው በራይዞም መሰረት ላይ ነው እንጂ ራይዞም አንድ ምዕራፍ ብቻ አይደለም ይላሉ ...

አዳም፡- እንደዛ ነው። የግርጌ ማስታወሻው ከዋናው ድርሰት ጋር በትርጉም ፣ ባዶ ቦታው ከስዕል ጋር ... ስለዚህ ስለ ስዕል ሳነሳ የይዘት በለው የቅርፅ ሜካኒዝም ነው። በሕጽዊነት ስለተገነባ መፅሐፉን ከፎቅ ላይ ብትጥላው በመሰረታዊ እሳቤው (metaphorically) አይበታተንም ... ገፆቹ ሳይበታተኑ ይገኛሉ .... ከአየሩም ሆነ ከመሬት ስበት ጋር ተያይዘው ይቆማሉ።

ተሻለ፡- የሰግር በሕጽናዊነት ንድፍ ሲመጣ ሕጽናዊነት ስግርን ይጠራል? ወይስ ሰግር ሕጽናዊነትን ይጠቀልላል?

አዳም፡- በየትኛውም ኑባሬ ውስጥ ሕጽን ይሰራል! ስግር የክዋኔ (performance) ጉዳይ ነው .... ራሱ ሕጽን የሆነ ሌላ ሕጽናዊነትን የሚፈጥር ነው። ራሱ መርበብትን የሚፈጥር (Network form) መርበብት (Network)ነው።

ተሻለ፡- ለምን መስለህ ለራይዞም ያደላሁት፣ አሁን ያለውን በሄግል እሳቤ የተዋቀረውን ዓለም (Heglian world) መሰረቶች እያፈረሳቸው ነው ብዬ ስለማስብ ነው ፤ ደግሞም የማፍረስ አቅም አለው። በተለይ የበይነ መረብ (Internet) መምጣት ዋነኛው ጉዳይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የፍልስፍና ጥያቄ መለወጡ ነው። አሁን ጥያቄው ሕይወት ምንድን ነው (What is Life? ) የሚለው አይደለም ጥያቄው ሕይወትን እንዴት ነው መኖር ያለብን (How might one live?) የሚለው ነው።

አዳም፡- ዘመኑ መሰረታዊ ከሚባሉት (Foundational) ጥያቄ ይበልጥ ወደ ተግባራዊ (Pragmatic) ጥያቄ ያደላል ወይም ሽግግር እያደረገ ነው። ስግር ስትሰራ ስድራት (Assemblege) የሚባል ሃሳብ አለ ... የሆኑ ንጥረ ነገሮች(Elements) ተሰባስበው የሚሰሯቸው የተወሰኑ ገጸ ባህርያት አሉ የተያያዙ ... ከዛ ውስጥ አንዱን ንጥረ ነገር ብታወጣ ያ' ንጥረ ነገር (Element) ተጠግተህ ብታየው ከብዙ ንጥረ ነገር (Elements) የተሰራ ነው። የስድራት(Assembledge) መርህን ለየት የሚያደረገው እዛ ንጥረ ነገር ውስጥ መርበብት (Network) አለ ፤ ስላልደረሰንበት ነው። ማለትም በቁስ ጥናት (Object Studies) ውስጥ ብዙ ፈላስፎች እንደሚሉት አንድ ቁስ (Object) ሙሉ ለሙሉ ራሱን አይሰጥም ... አንድን ቁስ (Object) ሙሉ ለሙሉ ማወቅ አንችልም። ሁልጊዜም አምቆ (retain) የሚይዘው ፣ ውስጡ የማንደርስበት ስሪት አለ ....በሂደት ልንደርስበት እንችላለን። ስለዚህ መሰረታዊ ሃሳብ (foundational idea) መገንባት አለብህ፣ መፍጠር አለብህ። እኔ የማደርገው ነገር ምንድን ነው? አዲስ አለም መፍጠር ከፈለግክ በትይይዝ አለማት ውስጥ አዳዲስ የትይይዝ መስመሮችን መፍጠር አለብህ ፤ እንግዳ ትይይዞችን ሳይቀር መፍጠር ያስፈልጋል (if you want to create a new world create other connections, strange connections) ። ያ' ንጥረ ነገር (Element) ስፍራው ሲለቅ (deterritorialize) አድርጎ ሌላ መኖሪያ (Village) ውስጥ ስትከተው ወይም አምጥተህ ሌላ ቦታ ስትተክለው አዲስ እመርታ (Emergent) ባህሪ ታገኛለህ።
ልክ እንደ ኬሚካል ፕሮሰስ ለምሳሌ ውሃ ($H_2O$) ብንወስድ የውህዱን ኢነርጂ በማስወጣት (Exotermic energy) አንዱን ኦክስጂን ወስደህ ከሌላ ንጥረ ነገር (Element) ጋር ለምሳሌ ከካርቦን ጋር መልሰህ ታዋህደዋለህ (Indotermic energy) ... ከዛም ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ($CO_2$) ማግኘት ትችላለህ። ልክ እንደዛው ለልብ ወለድም ይሰራል....

የሆነ ገጸ ባህርይን በሆነ ባልተነካ ጎኑ ሌላ እሳቤ ውስጥ ትከተዋለህ … እዚህ ጋር አባት ሆኖ ቢሆን እዛ አስተማሪ ይሆናል ፣ ስለዚህ በት/ቤት ስድራት (assemblage) አስተማሪ ይሆናል ፤ በቤተሰብ ስድራት (assemblage) አባት ይሆናል።
ተለምዷዊ በሆነው ነገር ውስጥ ግን ሰውየውን አንድ ገጸ ባህርይ ይሰ'ጠውና ያበቃል። ልብ ወለድ ከሆነ የአባት ገጸ ባህርይ ሰጥቶ ይጨርሰዋል። ሕጽናዊነት የሚያደርገው በስድራት (assemblage) ውስጥ የተለያዩ ግንኙነቶችን መፍጠር ነው።

ተሻለ፡- Hypertextuality, Interrelation,Medium, Intermediary የሚባሉ ሃሳቦች አሉ … አንድን ድርሰት ልዩ የሚያደረገው ከነበረበት ሚዲየም (Medium) ወጥቶ በሌላ ሚዲየም (Medium) ውስጥ መነበብ ሲችል ነው ይላሉ የዘርፉ አጥኚዎች ፤ እንደዛ መነበብ የሚችል ከሆነ ታላቅ ስራ ነው ያስብለዋል(the attributes of ultimate novel) ፤ ደረጃውም እጅግ የላቀ ይሆናል።
አዳም ፡- በሞዳሊቲ (Modality) ማለትም በሞድ (Mode) ለውጥ ውስጥ መገለጥ ወይም ህልውናው ማስቀጠል መቻል አለበት።

ተሻለ፡- ለምሳሌ ሰላማዊት ከማህሌት ወደ የሰንበት ቀለማት ስትመጣ አንድ ሰው ትራንስቴክስቹዋሊቲ (transtextuality) ነው ቢልና ሌላው ስፍራን መልቀቅ (deterritorialization) ነው ቢል ሁለቱም ልክ ይሆናሉ፤ ይሄ ምናልባት ምትሃት ይጠይቃል። ምክንያቱም ስራዎችህ ጥንታዊነትን ወደ ዘላለማዊነት የማሻገር አቅም ይሰጣቸዋል ፤ በመሆኑም ገጸባህርያቶችን ዘላለማዊነትን ያወርሳቸዋል የሚል እምነት አለኝ ….
አዳም፡- It’s all chain beings liberated ….I feel more…የመከፈት ነገር ይሰማኛል። ወሰን የለሽ በሆነ መልኩ ስፍራቸውን የመልቀቅ (infinitely deterritorialize) እና እንደገና የመስፈር (infinitely reterritorialize) ሰፊ እድል ስላላቸው እንደዛ ይመስለኛል።

ሀብቱ ፡- ሐበሻ የሚያደርግህ አንዱ ዘላለማዊነትን ለመውረስ ያለህ መሻት ነው ቢባል እውነት ነው?
አዳም፡- በል አጋባው ሃሃሃ …
ገዛኸኝ፡- የዚህን ቤት ኬክ ሳትቀምሰው ልትሄድ ነው?
አዳም፡- አክስቱን ባቅላቫን በላኋት እኮ ሃሃሃ ….
ሀብቱ፡- ሸንኮሬን?
አዳም፡- ሸንኮሬን አዎ! ሁለችንም ሳቅን …

በጨዋታና በሳቅ ተሞልተን ሳናውቀው ጊዜው  አለቀብን። ከካፌው ወጥተን  ጋዜቦ አደባባይ ላይ ቋሚ ምስክር ለማስቀረት አብረነው ፎቶ ተነሳን። ሐብቱም አንዴ በቀኙ በኩል ፎቶ አንሱኝ አለ። ለምን በቀኙ? ቀኝ እጁን እኔ ቀድሜ እንዳስገርኩት ሐብቱ አልጠረጠረምና እነሱ እየተነሱ እኔ ፈገግ አልኩ! ጨዋታ አዋቂው ሰው ለመለያየት ቻው ስንባባል እንኳ  ጨዋታውን አላቋረጠምና ሐብቱን “ቀጣይ ስመጣ ፀጉርህ አፍሮ አድርገህ እንዳገኝህ ሃሃ”  ብሎ ተረበው" አንተ ወጣት ኾነህ የምትመጣልን ከኾነ" መለሰ ሐብቱ፤ ቢቻል ቢቻል ለዘላለም በወጣትነቱ የሚያጸኑት ሰው ነው— አዳም። እንዲህ እንዲህ ተሳስቀን ወደ ቤቴል የሚወስደው የራይድ ታክሲ ውስጥ አስገብተን ተሰናበትነው፤ ጊዜያዊ ስንብት።  በርግጥ ግን ስንብት ነው? እሱን መሰናበት ይቻላል? ቤታችን፣ ልባችንና አእምሯችን ውስጥ ላይጠፉ የተሳሉ ሐሳቦቹ፣ተረኮቹ፣ ፍልስፍናዎቹ፣ ሐርነት አውጭ ፈጠራዎቹ የት ሄደው ተሰናበት ነው እንለዋለን?
አሁንስ መዝሙረ ሄላምን እየጠበቅን አይደለምን?